742/2013 54

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT & HOUSING

ቁጥር 8/000 ... /119
Ref.
ቀን 5/11/2008
Date
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - ETHIOPIA

**ለፌዴራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና**

**የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ**

**አዲስ አበባ፣**

**ጉዳዩ፣ የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያን ይመለከታል፣**

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒ ካቢኔ ሰኔ 30/2008 ዓ/ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ በኤጀንሲው የቀረበውን የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ ረቂቅ በዝርዝር ከተመለከተ እና ከተወያየበት በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ከሐምሌ 01/2008 ዓ/ም ጀምሮ የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ ቁጥር 54/2008 ሆኖ እንዲፀድቅ የተወሰነ ስለሆነ መመሪያው የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በሚተገበርባቸው ከተሞች በጥንቃቄ እና በኃላፊነት ስሜት ተግባራዊ እንዲሆን አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

**ግልባጭ፣**

- ለኢፌዲሪ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር
- ለኢፌዲሪ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
  **አዲስ አበባ**
- ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
- የከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ
- ለቤቶች ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ
  **ከ/ል/ቤ/ሚ/ር**

ስልክ TEL 011-553 16-88 011-553 16 72 011-553-1673
ፖ.ሳ.ቁ P.O.Box 24134/1000
ፋክስ / Fax 011-554 12-68
ድረ ገጽ / Web.Site www.mudc-gov.et
E-mail: wud-sm@ehtionet.et

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የከተሞች ምግብ ዋስትና ፕሮግራም የተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ ቁጥር 742/2013

ሐምሌ/ 2008 ዓ.ም

# አዲስ አበባ

## ማውጫ

ገጽ


መግቢያ ....2
ክፍል አንድ ....3
1. አጭር ርዕስ ....3
2. ትርጓሜ ....3
2. የመመሪያው ዓላማ ....4
3. የተፈፃሚነት ወሰን ....5
4. የተጠቃሚዎች መመልመያ መርሆች ....5
ክፍል ሁለት ....5
5. የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ....5
6. የተጠቃሚዎች ምልመላን በሚመለከት የአስፈጻሚና የባለድርሻአካላት ተግባርና ሃላፊነት፣ ....9
7. የክትትል፣ የሪፖርትና የግምገማና ስርዓት፣ ....12
ክፍል ሶስት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ....13
8. የበጀት ምንጭ ....13
9. የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ የሚከናወንበት ጊዜ ....13
10. ተጠያቂነት ....13
11. መመሪያውን ስለ ማሻሻል ....13
12. ተቀባይነት የማይኖራቸው ሕጎች ....13
13. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ....13


በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር * The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

## መግቢያ

በከተሞች የሚገኘውን የስራ አጥነትና ድህነት ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ እና ወደ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ ሀገራችን ራዕይ ሰንቃ ጉዞ ጀምራለች፡፡ ይህንኑ ለማስፈጸም በርካታ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን በከተሞች እየተተገበረ ያለው የስራ ዕድል ፈጠራ፣ የቤቶች ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ የተመዘገቡት ውጤቶች አመርቂ ናቸው፡፡ በከተሞች እየተከናወነ ካለው የስራ ዕድል ፈጠራ ጎን ለጎን ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መንግስት የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂና ፕሮግራም ቀርጾ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በዋናነኝነት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በተለይም በከተሞች አካባቢ የሚታዩ በድህነት ውስጥ የሚገኙ እና ለተለያዩ የማህበራዊ ችግርና ጠንቅ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ወደ ትግበራ ምዕራፍ ለመግባት ከሚሰሩት ዋነኛ ስራዎች መካከል ተጠቃሚዎችን በቤተሰብ ደረጃ መለየት አንዱ ሲሆን የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን ከኪራይ ሰብሳቢነት በጸዳ እና ግልጽነትና ተጠያቂነት ባሰፈነ መልኩ ለመለየት የቤተሰብ ተጠቃሚዎች የመመልመያ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ በፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መቋቋሚያ ደንብ 374/2008 አንቀጽ 14 መሰረት ሚንስቴሩ ደንቡን ለማስፈጸም የሚያስችል በደንብ ላይ በተቀመጠው መሰረት ይህ የተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia * Ministry of Urban Development & Housing

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ ቁጥር 742/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1) **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
2) **"ኤጀንሲ"** ማለት የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፤
3) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያው ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
4) **"ከተማ"** ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ፡ 2,000 እና ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ ላይ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፤
5) **"የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ"** ማለት መጠን እና ጥራትን ባማከለ መልኩ በዘላቂነት ምግብ በማግኘት የእያንዳንዱ ግለሰብ የነፍስ ወከፍ የዕለት ፍጆታን እስከ 2,200 ካሎሪ እንዲደርስ እና የተመጣጠነ የስርዓተ ምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ በማድረግ ጤናማና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ ነዉ፡፡
6) **"የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ጠቃሚ"** ማለት በከተሞች ምግብ ዋስትና ፕሮግራም በቤተሰብ ደረጃ ከተለየ በኋላ በአካባቢ ልማት ስራዎች፤ በቀጥታ ድጋፍ እና በኑሮማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች የሚሳተፍ ቤተሰብ ነው፡፡
7) **"ምልመላ"** ማለት በከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በቀጥታ ድጋፍ ፡በአካባቢ ልማት ስራዎች እና በኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ የሚሆኑ ቤተሰቦችን የመምረጥ ሂደት ነው፡፡
8) **"ህጋዊ ማስረጃ"** ማለት ዕድሜን፡ ነዋሪነትን፡ የአካል ጉዳትን፡ ህመምን፡ ሞትን እንዲሁም የመስራት ብቃትን አስመልክቶ ከሚመለከተው አካል የሚሰጥ 6 ወር ያላለፈው ማስረጃ ነው፤
9) **"አረጋውያን"** ማለት ጠሪና ደጋፊ የሌላቸው ዕድሜያቸው 60 አመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ማለት ነው፤

10) **"ምክር ቤት"** ማለት የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ለመምራት የተቋቋመ ምክር ቤት ነው፡፡

11) **"የቀጥታ ድጋፍ"** ማለት በተደራራቢ የአካል ጉዳት እና በእድሜ ምክንያት ሰርተው ገቢ ለማግኘት የማይችሉ በቤተሰብ ደረጃ ከተለየ በኋላ በፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሚሆኑ በቀጥታ በገንዘብ ወይም በዓይነት ድጋፍ የሚሰጥበት የድጋፍ ዓይነት ነው፡፡

12) **"የአካባቢ ልማት ስራዎች"** ማለት የአካባቢው አስተዳደርና በህብረተሰቡ የሚታቀዱ የአረንጓዴ ልማት፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የወንዞች ዳርቻ ልማት፣ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በመስራት ገቢ ለማግኘት የሚያስችል የሥራ ዓይነት ነው፡፡

13) "ዘላቂ **የኑሮ ማሻሻያ"** ማለት በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች ወይም ግለሰቦችን በራሳቸው ጥረት ኑሮቸውን እንዲያሻሽሉ የሚሰጥ የድጋፍ ዓይነት ነው፡፡

14) " **የቀጠና ልማት ኮሚቴ"** ማለት በመኖሪያ አካባቢ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች ተውጣጥቶ በቀጠና ልማት ላይ የሚመክር የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን የሚያስተባብር በኗሪው የሚመረጥ የኮሚቴ አደረጃጀት ነው፡፡

15) **"ሽግግር"** ማለት የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ከአንደኛው የድጋፍ ዓይነት ወደ ሌላኛው የድጋፍ ዓይነት አስፈላጊውን መስፈርት በሟሟላት የማስተላለፍ ሂደት ነው፡፡

16) **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው እና ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የመንግስት አካላት፣ የልማት አጋሮች፣ ተጠቃሚዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎች ማለት ነው፡፡

17) **"ቀጠና" ማለት** ከወረዳ በታች ያለ የአስተዳደር እርከን ነው፣

18) **"ሰው "** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

19) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል::

## 2. የመመሪያው ዓላማ

በከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉትን ቤተሰቦች ተጠቃሚ ለማድረግ በአካባቢ ልማት ስራዎች፣ በዘላቂ ኑሮ ዋስትና እና በቀጥታ ድጋፍ አማካኝነት የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ እና ከድህነት እንዲወጡ የሚያስችል የመመልመያ ስርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Housing

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚተገበረው የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በአካባቢ ልማት ስራዎች፣ በኑሮ ማሻሻያና በቀጥታ ድጋፍ ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች መመልመያነት የሚያገለግል ይሆናል፡፡

## 4. የተጠቃሚዎች መመልመያ መርሆች

1) የጠባቂነትን አመለካከት መቅረፍ፣
2) የማህበራዊ ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦችን በፍትሃዊነት የመጠቀም መብትን ማረጋገጥ፣
3) ግልጽነትና ተጠያቂነት፣
4) የህብረተሰብ ተሳትፎን ማጠናከርና ከሌሎች የልማት ስራዎች ጋር ማስተሳሰር፣
5) ተከታታይነት ያለው መማማር፣
6) ሃብትን በተገቢው መንገድ መጠቀም፣
7) የተጠቃሚዎችና የባለድርሻ አካላትን መረጃ የማግኘትን መብት ማክበር፣
8) ምስጥር መጠበቅ፣

# ክፍል ሁለት

# የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች፣ የመመልመያ ዘዴ፣

# መስፈርትና የምዝገባ ሥርዓት

## 5. የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች

1) የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ እና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ከእነዚህም የህብረተሰብ ክፍሎች፡-

ሀ) ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ፤
ለ) ጎዳና ተዳዳሪዎች፤
ሐ) ለምኖ አዳሪዎች፣
መ) ሴተኛ አዳሪዎች፣
ሠ) ስራ አጥ ዜጎች፣
ረ) አካል ጉዳተኞች፤
ሰ) የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች፣
ሸ) አረጋውያን፤
ቀ) ህጻናት ያካተተ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

2) **የተጠቃሚዎች መመልመያ ዘዴዎች**

በሀገሪቱ የሚከናወኑ የተጠቃሚዎች ምልመላ ስርዓት ከገጠር የልማታዊ ሴፍቲኔት ምልመላ ስርዓት ጋር ቁርኝት ያለው እና የከተሞችን ልዩ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የፕሮግራም ተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ በዋነኝነት፡-

ሀ) በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ፣

ለ) ቀጠና ኮሚቴዎች፣

ሐ) የቡድን፣

መ) የኑሮ ደረጃ ምዘና፣

ሠ) እራስን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ለፕሮግራሙ እጩ በማድረግ፣

ረ) ከላይ ከተመለከቱት ሊጣጣሙ ከሚችሉ ሁለትና ከዚያ በላይ መመዘኛዎችን በጣምራ በመጠቀም የተጠቃሚዎች ምልመላ የሚከናወን ይሆናል፡፡

3) **በተጠቃሚዎች ምልመላ የሚሳተፉ አካላት**

ሀ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ ሂደት ላይ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ህዝባዊ አደረጃጀቶች፣ እድሮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የፍትህ አካላትና ሌሎች ባለድርሻና ተባባሪ አካላት በቀጠና ደረጃ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

ለ) በየደረጃው የሚገኙ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች እና የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤቶች በጋራ በመቀናጀት ቀጠናዎችን በመለየት ከቀጠና ም/ቤት ጋር በመሆን የቀጠና ምልመላ ኮሚቴ አባላትን በማስመረጥ ከየቀጠናው የሚመረጠውን ተጠቃሚ ቤተሰቦች በመወሰን፣ የተጠመረጡትን ተጠቃሚዎች ለህብረተሰቡ የማሳወቅ ተግባር ያከናውናሉ፣

ሐ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች አመራረጥ ላይ ህብረተሰቡና ተጠቃሚዎች ቅሬታ የሚያቀርቡበት የአሰራር ሰርዓት በመዘርጋት በስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

4) **የተጠቃሚዎች መመልመያ መስፈርት፣**

የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ የሚመከተሉት መስፍርቶች ይኖሩታል፣

(1) **የከተማ መምረጫ መስፈርቶች ከመቶኛ፣**

ሀ) የከተሞች የድህነት ወለል(25)፣

ለ) በከተሞች የሚኖሩ የህዝብ ቁጥር (20)፣

ሐ) የከተሞች የስራ አጥነት ምጣኔ (20)፣

መ) በከተሞች የማህበራዊ ኑሮችግር እና የአደጋ ተጋላጭነት(10)፣

ሠ) የከተሞች የዕድገት ደረጃ፣ (ከተሞች በየፈርጃቸው የሚወዳደሩ መሆኑን(10)፣

ረ) ከተሞች ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ ያላቸው ዝግጁነት(10)፣

The Federal Democratic Republic of Ethiopia * Ministry of Urban Development & Housing *

ሰ) ከገጠር ወደ ከተማ፣ ከከተማ ወደ ከተማ፣ከሀገር ወደ ሀገር ያለው የፍልሰት መጠን(5)፣

**(2) የቀጠና መምረጫ መስፈርቶች ከመቶኛ፣**

ሀ) ከድህነት ወለል በታች ያሉ ቤተሰቦች ብዛት(25)፣

ለ) የስራ አጦች ብዛት(20)፣

ሐ) የማህበራዊ ኑሮ ችግር ተጋላጮች ብዛት (15)፣

መ) ለአ.- መደበኛ ስራዎች ተጋላጭ የሆኑ ሰፈሮች (10)፣

ሠ) ለሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች የተጋለጡ ሰፈሮች(10)፣

ረ) ሌሎች የልማት ፕሮግራሞች በብዛት የማይገኙባቸው ሰፈሮች(8)፣

ሰ) የመሰረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ሽፋን(6)፣

ሸ) ሰፈር ውስጥ ያሉ የመኖሪያ ቤቶች ሁኔታ(6)፣

**(3) የተጠቃሚ ቤተሰቦችን የመምረጫ መስፈርቶች ፣**

ሀ) አማካኝ የነፍስ ወከፍ ገቢው በቀን ከ 2 ዶላር በታች የሆነ መሆኑ፣

ለ) ፕሮግራሙ በሚተገበርበት ቀጠና ለ6 ወር እና ከዚያ በላይ መኖሩ፣

ሐ) በፕሮግራሙ ለመሳተፍ የሚያበቃዉን መስፈርት ማሟላቱን በቀጠና ልማት ኮሚቴ ተመልምሎ የሚገባዉ መሆኑን የተረጋገጠ ከሆነ፣

መ) በሌሎች የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት እና የእርዳታ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ያልሆኑ ቤተሰቦች ፣

**5) በአካባቢ ልማት ስራዎች ንዑስ ፕሮግራም የሚሳተፉትን ቤተሰቦች መመልመያ መስፈርቶች ፣**

ሀ) ከድህነት ወለል በታች ሆነዉ የመሥራት አቅም ያላቸው፣

ለ) ከድህነት ወለል በታች የሆኑ ስራ አጦች መሆናቸው የተረጋገጠ፣

ሐ) ከ18 ዓመት በላይ የሆነው የቤተሰቡ አባልና በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆነ፣

መ) ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ እስከ አራት የቤተሰብ አባላት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፣

ሠ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ሆነው ወለደው የሚያጠቡ እናቶችና ነፍሰ ጡር ሴቶች ሊተካቸው የሚችል የቤተሰብ አባል ካለ ሊተኩ ይችላሉ፣

6) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 ከተራ ፊደል ሀ እስከ ሠ የተዘረዘሩት መስፍረቶች የሚታቀፉ ተጠቃሚዎች የጉልበት ክፍያ በአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ የሚወሰን ሆኖ ከሚያገኙት ዕለታዊ ገቢ 80 በመቶው ለፍጆታ የሚውሉት ሲሆን 20 በመቶውን እንዲቆጥቡ በማድረግ ከፕሮግራሙ 40 በመቶ ተጨማሪ ድጋፍ በቁጠባቸው በባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

7) **የቀጥታ ድጋፍ ንኡስ ፕሮግራም የተጠቀሚዎች መመልመያ መስፈርቶች፣**

ሀ) ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን እና ወላጅ አልባና ደጋፊ የሌላቸው ሕጻናት፣

ለ) በህመም ምክንያት ራሳቸውንም ሆነ ልጆቻቸውን ሰርተው ማስተዳደር የማይችሉ ቤተሰቦች፣

ሐ) በተደራራቢ አካል ጉዳት ምክንያት መስራት የማይችሉ እና ደጋፊ የሌላቸው አካል ጉዳተኞች፣

መ) የሚደግፋቸው ቤተሰብ የሌላቸው በኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ ምክንያት የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ዜጎች፣

በዚህ ንኡስ ፕሮግራም ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች በራሳቸው ወይም በሚወክሉት ሰው አማካኝነት የባንክ ሂሳብ ተከፍቶ በየወሩ ብር 170 ገቢ ይደረግላቸዋል፡፡

8) **የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሙ የሚሳተፉትን ቤተሰቦች መመልመያ መስፈርቶች፣**

ሀ) የመሥራት አቅም ያላቸው እና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ቤተሰቦች ሆነው በአካል ችግር ወይም በሌላ በአካባቢ ልማት ስራዎች ለመሳተፍ የማይችሉ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) በአካባቢ ልማት ስራዎች ተሰማርተው አስፈላጊው የቁጠባ መጠን ያላቸው፣

ሐ) ከቤተሰቡ አባል አንዱ ስልጠና ለመውሰድ ዝግጁ የሆነና አዋጭ ቢዝነስ ፕላን ማቅረብ የሚችል፣

መ) በኢ- መደበኛ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙና ወደ ህጋዊ አሰራር ለመግባት ፍቃደኛ የሆኑ፣

ሠ) መንግስት የሚያመቻቸውን ድጋፍ በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል ዝግጁ የሆነ፣

ረ) መንግስት የሚፈጥርለትን የስራ ትስስር በአግባቡ ለመጠቀም ዝግጁ የሆነ፣

ሰ) የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ ኢንተርፕራይዝ ለመመስረት ዝግጁ የሆነ፣

በዚህ ንኡስ ፕሮግራም ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች በባንክ ሂሳባቸው ብር 10000 (አስር ሺ) ለስራ ማስጀመሪያ ሚሆን መነሻ ኮፒታል ገቢ ይደረግላቸዋል፡፡

9) **ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ስርዓት ዝርጋታን በተመለከተ፣**

ሀ) የሶስቱም ንዑስ ፕሮግራሞች መረጃዎች በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት የታገዙ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

ለ) የመረጃ ስርዓቱ የተጠቃሚውን ጥሬ ሀቅና የቀረበለትን ድጋፍ ዓይነት በዝርዝር የሚያሳይ ይሆናል፣

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

ሐ) መረጃው በየደረጃው በሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ተደራጅተው በወቅቱ ለሚመለከተው አካል እንዲደርሱ ይደረጋል፣

## 10) የጎዳና ነዋሪዎች ምዝገባና ተጠቃሚነት፣

የጎዳና ነዋሪዎች በባህሪያቸው ተንቀሳቃሽና የተወሰነ የመኖሪያ አድራሻ የሌላቸው በመሆኑ ልዩ የምዝገባ ዘዴ መጠቀም ተገቢ ይሆናል፡፡ የማደሪያ ቦታዎችን መለየት እና የተደራጀ መረጃ መያዝ ፡ ስለ ፕሮግራሙ ዓላማ ማወያየት እና በቂ ግንዛቤ መፍጠር፣ ለተለዩ ተጠቃሚዎች እንደየ ተጠቃሚዎቹ አይነት የስነ ልቦና ስልጠና መስጠት፣ የሚሳተፉበትን የንዑስ ፕሮግራም እንዲለዩ ማድረግ፣ በአሻራና በፎቶ የተደገፈ ምዝገባ አመቺ በሆነ ጊዜ ማካሄድ እና ወደ በመረጧቸው ንዑስ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

## 6. የተጠቃሚዎች ምልመላን በሚመለከት የአስፈጻሚና የባለድርሻአካላት ተግባርና ሃላፊነት፣

### 1) የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

ሀ) የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ በማጽደቅ ተግባሪዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

ለ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መመሪያ አፈጻጸምን ይከታተላል ፡ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

### 2) የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

ሀ) ከአስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መመሪያ ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል፣ ያሰራጫል፣

ለ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ ዙሪያ ዕቀድ ያዘጋጃል፣ ለምልመላ ስራ አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ያመቻቻል፣

ሐ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ ዙሪያ የቴክኒክ ድጋፎችን ያደርጋል፣

መ) በተጠቃሚ ቤተሰቦችን መሰረት ያደረገ የመረጃ ቋት ያደራጃል፣ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

ሠ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች ቅሬታ መፈታቱን ይከታተላል፣ የመፍትሄ አቅጣጫም ይሰጣል፣

ረ) የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲስፉ ያደርጋል፣

ሰ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ አፈጻጸምን በጋራ ይከታተላል ፡ ይገመግማል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፣ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

### 3) ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

ሀ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መመሪያ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ ያደርጋል፣

ለ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ ዙሪያ ዕቀድ ያዘጋጃል፡ ለምልመላ ስራ አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡

ሐ) ለጎዳና ነዋሪዎች፡ ለሴተኛ አዳሪዎችና ለለምና አዳሪዎች የስነ ልቦና ትምህርት በመስጠት በምግብ ዋስትና ፕሮግራም እንዲታቀፉ በጋራ ይሰራል፡

መ) በቀጥታ ድጋፍ በተጠቃሚ ቤተሰቦች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡

ሠ) የቀጥታ ድጋፍ በተጠቃሚ ቤተሰቦች መረጃ በየክልሉና በተዋረድ ባሉ ጽ/ቤቶች በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፡

ረ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች ቅሬታ መፈታቱን ይከታተላል፡ የመፍትሄ አቅጣጫም ይሰጣል፡

ሰ) የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎችን ምልመላ በሚመለከት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራል፡ ያሰራጫል፡

## 4) የክልል እና ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎች

ሀ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መመሪያ ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ፡

ለ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ ዙሪያ በተዋረድ ላሉ አደረጃጀቶች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፡

ሐ) በየደረጃው ተጠቃሚ ቤተሰቦች በመመሪያው መሰረት መለየታቸውንና መመዝገባቸውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፡

መ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋ ያደርጋሉ፡

ሠ) የተጠቃሚዎችን መረጃ በአግባቡ ይሰበስባሉ፡ ያደራጃሉ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ ያደርጋሉ፡

ረ) በየደረጃው ለቀረቡ ቅሬታዎች መፍትሄና ግብረ መልስ ይሰጣሉ፡

ሰ) በአፈጻጸም ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን እና ጠንካራ ጎኖችን በጋራ ይገመግማሉ፡ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፡

ሸ) አፈጻጸሙን ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡

## 5) የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች

ሀ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ መስፈርቶች ዙሪያ ግብአት ይሰጣሉ፡

ለ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ መመሪያ ላይ ለወረዳዎች እና ለቀጠናዎች ጣቢያዎች ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፡

ሐ) በየደረጃው ተጠቃሚ ቤተሰቦች በመመሪያው መሰረት መመልመላቸውንና መመዝገባቸውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፡

መ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች መረጃን በአግባቡ ይሰበስባሉ፣ ያደራጃሉ እንዲሁም ለሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋሉ፣

ሠ) በየደረጃው ለቀረቡ ቅሬታዎች መፍትሄ ይሰጣሉ፣

ረ) በአፈጻጸም ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን እና ጠንካራ ጎኖችን በጋራ ይገመግማሉ፣ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፣

ሰ) አፈጻጸሙን ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያደርጋሉ፣

## 6) የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ

ሀ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መስፈርት ላይ አስተያየት ይሰጣል፣

ለ) የቀጠና ምልመላ ኮሚቴ እና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል፣

ሐ) ስለ ምልመላ መመሪያና አፈጻጸም ለቀጠና ኮሚቴና ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ ይፈጥራል፣

መ) በኮሚቴው አማካኝነት ተጠቃሚ ቤተሰቦች እንዲመለመሉና እንዲመዘገቡ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

ሠ) የተጠቃሚ ቤተሰቦችን መረጃ በአግባቡ ይይዛሉ፣ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣

ረ) ለተጠቃሚ ቤተሰቦች ቅሬታ ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣሉ፣ ከአቅም በላይ የሆኑትን ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣

ሰ) ተዘዋዋሪ ለሆኑ ተጠቃሚ ቤተሰቦች በቋሚነት በፕሮግራሙ የሚታቀፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሸ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ አፈጻጸም ዙሪያ የጋራ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

## 7) የቀጠና ልማት ኮሚቴ

ሀ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መስፈርት ላይ አስተያየት ለሚመለከተው አካል ይሰጣሉ፣

ለ) ስለ መመልመያ መስፈርት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፣

ሐ) የቤት ለቤት ምዝገባን ያከናውናሉ፣

መ) የተመዘገቡትን ተጠቃሚ ቤተሰቦች የህዝብ መድረኮች በማመቻቸት ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ፣ ህዝቡም አስተያየት እንዲሰጥበት ያደርጋሉ፣

ሠ) የተጠቃሚ ቤተሰቦችን ቅሬታ በመለየት አስፈላጊውን ምላሽ ይሰጣሉ፣

ረ) ተጠቃሚ ቤተሰቦች እንደየመስራት አቅማቸው በአካባቢ ልማት ሰራዎች፣ በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያና በቀጥታ ድጋፍ ይለያሉ፣

ሰ) የአካባቢ የልማት ስራዎችን በጋራ ይለያሉ፣

ሸ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች መረጃ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋሉ፣

## 7. የክትትል፣ የሪፖርትና የግምገማና ስርዓት፣

1) **የክትትልና ድጋፍ ስርዓት፣**

ሀ) የፌዴራል የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ለፕሮግራሙን ስኬታማነት በየወሩ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ከተሞች በአካል በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ለ) የክልል / የከተማ አስተዳደር የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ለፕሮግራሙን ስኬታማነት በየአስራ አምስት ቀን ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ከተሞች በአካል በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ሐ) የከተማ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ለፕሮግራሙን ስኬታማነት በየሳምንቱ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት በአካል በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

መ) የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት ለፕሮግራሙ ስኬታማነት በየቀኑ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ቀጠና ላይ በአካል በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

2) **የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት**

ሀ) የቀጠና ኮሚቴ የፕሮግራሙን አፈጻጸም በሚመለከት በየቀኑ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት የጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባል ፤

ለ) የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት የፕሮግራሙን አፈጻጸም በሚመለከት በየሳምንቱ የጽሁፍ ሪፖርት ለከተማ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ያቀርባል ፤

ሐ) የከተማ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት የፕሮግራሙን አፈጻጸም በሚመለከት በየአስራ አምስት ቀኑ የጽሁፍ ሪፖርት ለክልሉ/ለከተማ አስተዳድሩ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ያቀርባል፣

መ) የክልሉ/ የከተማ አስተዳድሩ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የፕሮግራሙን አፈጻጸም በሚመለከት በየወሩ የጽሁፍ ሪፖርት ለፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ያቀርባል፣

# ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 8. የበጀት ምንጭ

የከተሞች የምግብ ዋስትና የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ክፍያዎች የሚፈፀሙት በፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በኩል ለከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ከተመደበው በጀት የሚከፈል ይሆናል፡፡

### 9. የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ የሚከናወንበት ጊዜ

የተጠቃሚዎች ምልመላ በዓመት አንድ ጊዜ በጣት አሻራ እና በፎቶ ግራፍ በማስደገፍ በ1ኛው ሩብ ዓመት የሚከናወን ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በማንኛውም ጊዜ የሚከለስ ይሆናል፡፡ ለተጠቃሚ ቤተሰቦችም የመለያ ቁጥርና መታወቂያ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡ ምዝገባውም በሃገር አቀፍ ደረጃ ፕሮግራሙ በሚጀመርባቸው ከተሞች በተመሳሳይ ወቅት የሚከናወን ይሆናል፡፡

### 10. ተጠያቂነት

1) ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም ተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋ፤
2) ኃላፊነትን የማይወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ወይም የፐብሊክ ሰርቪስ ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፤

### 11. መመሪያውን ስለ ማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ለሚኒስቴር አቅርቦ የሚያሻሻል ሆኖ ክልሎችም በፌዴራሉ እውቅና ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

### 12. ተቀባይነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 13. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

---------------------------------

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

ሚኒስትር